# Ways of Gaining Provision from Allah

# ከአሏህ ስንቅ ወይም ሲሳይ የምናገኝባቸው መንገዶች



ትርጉም: በአህመድ የሱፍ

## Presented by Youth-Mission Online Amharic Books publishing.

# Ways of Gaining Provision from Allah

# ከአሏህ ስንቅ ወይም ሲሳይ የምናገኝባቸው መንገዶች

በአህመድ የሱፍ

**All right reserved**

© የወጣቱ ተልዕኮ

የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008

ሰሜን ወሎ ወልዲያ

ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323

http://youth-mission.mobie.in

ዘመኑ የውድድርና የሽቅድድም ዘመን በመሆኑ የሰው ልጅ ሩጫው ለዱንያና ዱንያ ለያዘችው ነገር ሆኗል። ሆኖም በአሁኑ ወቅት ሰዎች ስራ ማጣት ፣ በቂ ገቢ አለማግኘት ፣ እራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ነገር አለማግኘት ፣ ትዳር መስርተው የሚኖሩበት ወይም ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት በቂ ሲሳይ ማጣት ያስጨንቃቸዋል። ሆኖም ይህን ችግር ለማስወገድ በአሏህ መንገድ ላይ ሆነው ከመፈለግ ይልቅ ሃራም የሆኑ የለውጥ ጎዳናዎችን ሲጠቀሙ ይስተዋላል።

በዚች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት ቀናውን የአሏህ መንገድ ተከትለን ሲሳይ ማግኘት እንደምንችል ከቁርአንና ከሐዲስ ማስረጃዎችን በማጣቀስ የተወሰኑ ጠቃሚ ነጥቦች ተዳሰዋል። መልካም ንባብ!

# ከአሏህ ስንቅ ወይም ሲሳይ የምናገኝባቸው መንገዶች

**በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።**

የአሏህ ሰላትና ሰላም የነብያቶችና የመልዕክተኞች መደምደሚያ በሆኑት ነብያችን ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ላይ ፣ በቤተሰቦቻቸውና በሱሃቦቻቸው ላይ ሁሉ ይሁን።

በአሁኑ ወቅት ብዙ ሰዎች ስለ ሲሳያቸው መቀነስ ወይም በረካ ማጣት እንዲሁም እየገጠማቸው ስላለው ፈተና ሲያማርሩ ይስተዋላል። ይህ ልባቸውና አዕምሯቸው ላይ ነግሶ እረፍት ይነሳቸዋል። ታዲያ ይህን ለማስወገድ የተሻለ ነው ብለው የሚያስቡትን አቋራጭ የለውጥ ጎዳና ይጠቀማሉ። ለምሳሌ አንዳንዱ ሰው ቤተሰቡን ለማስተዳደርና ልጆቹን ለማሳደግ የሚሆነውን ገቢ ለመጨመር አራጣ ሲበላ ፣ አንዳንዱ ጉቦ ይበላል ሌላው ደግሞ ይዋሻል ያጭበረብራል ወ.ዘ.ተ

ታዲያ እነዚህን ሁሉ ሃጢያቶች የሚፈፅሙት ፍላጎታቸውን የሚያሟሉበት መንገድ መስሎ ስለሚሰማቸው ነው። በእርግጥ እንዲህ ብለው የሚያስቡና የሚሰሩ ከሆነ የአሏህን ሲሳይ የሚያገኙበትን መልካም ጎዳና ረስተዋል ማለት ነው። በእርግጥ ቀናውን መንገድ ተከትለው የአሏህን ሲሳይ ለሚሹ ሰዎች በርካታ ሲሳይና ከለላ ፍፁም ባላሰቡት መልኩ እንደሚሰጣቸው አሏሁ አዘወጀል ቃል ገብቷል።

ውድ ሙስሊም እህት ወንድሞቼ! የሚከተሉት ነጥቦች ቀናውን ጎዳና ተከትለን ከአሏህ ሲሳይ ወይም ስንቅ የምናገኝባቸውን መንገዶች የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

**1 ተቅዋ**

አሏህ እሱን መፍራት ሲሳያችነን የምናገኝበት ወይም የምንጨምርበት መንገድ አድርጎታል፡፡ አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አልቁርአን 65:2-3})>=**

**{2} አሏህንም የሚፈራ ሰው (ለችግሩ ሁሉ) መውጫውን ያደርግለታል፡፡**

**{3} በፍፁም ካላሰበው በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፡፡ በአሏህም ላይ የሚመካ እሱ በቂው ነው፡፡ በእርግጥ አሏህ ለሁሉም ነገር የተውሰነ ጊዜን አድርጓል፡፡**

ከእኛ መካከል አሏህን ለሚፈሩና በማንኛውም ሁኔታ ላይ እሱን ለሚያስደስቱ ነገሮች ጥንቁቆች ለሆኑ በዱንያና በመጭው አለም ህይወት ይመነዳቸዋል፡፡ ከአለማዊ ምንዳዎች አንደኛው አሏህ ከመከራና ከችግር የምንወጣበትን ጎዳና የሚያበጅልን መሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ባላሰብነው መንገድ ያስገኘናል፡፡ አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን7:96})>=**

**{96} የመንደሩ ሰዎች ባመኑና በፈሩ (ተቅዋ በኖራቸው) ኖሮ በእነሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር። ግን አስተባበሉ። ይሰሩት በነበሩትም ሃጢያት ያዝናቸው።**

ሸኽ አሰአዲ ከዚህ ጋር አያይዘው ከልባቸው በቅንነት ቢሚያምኑና እምነታቸውን በተግባር ቢያረጋግጡ እንዲሁም ከውጭም ከውስጥም በኩል አሏህን ቢፈሩ ኖሮ አሏህ ከሰማይ ዝናብን እንዲጥል በማድረግና ከመሬት እነሱና ከብቶቻቸው የሚጠቀሙበት የሆነን እፅዋት እንዲበቅል በማድረግ በረካውን ይከፍትላቸው ነበር። የብልፅግና ህይወትንም ያለምንም ችግርና ድካም ይኖሩ ነበር ሲሉ ተናግረዋል።

አሏህ ከእሱ ሲሳይን ከማግኘት ጀርባ ምክኒያት ያደረገው ይህ ተቅዋ ምንድነው? አሏህን ፈሪ ለሆኑ ሰዎች ቁጥር ስፍር የለሽ ሲሳይን የሚሰጣቸው መሆኑን ለምን አሳወቀን?

ተቅዋ እኛንና እኛን ሊጎዱን በሚችሉ ነገሮች መካከል ላይ ያለ ገደብ ነው። አሏህ እንድንሰራ ያዘዘንን ማንኛውንም ነገር በመስራትና አሏህ ከከለከለን ማንኛውም ነገሮች በመራቅ መልክ የመጣ መጠበቂያም ነው። በእርግጥም ህይወታችን በነዚህ ሁለት ነገሮች ዙርያ ነው የምታጠነጥነው። ተቅዋን በመግለፅና በማብራራት ዙርያ ቀደምቶች የተናገሯቸው በርካታ አባባሎች ቢኖሩም ለጊዜው አንዱን እንመልከት።

ኢብን መስኡድ(ረ.ዐ) ተቅዋ ማለት አሏህን መታዘዝና በፍፁም በእሱ ላይ አለማመፅ፤ እሱን ማስታወስና አለመርሳት፤ እሱን ማመስገንና አለመካድ ነው ብሏል።

ውድ ሙስሊም እህት ወንድሞቼ! እውነት ሲሳይ ለማግኘት ፣ ወይም ሲሳያችን እንዲጨምርልን ፣ ለአኺራ ስንቅ ለመያዝ ፣ ምቹና የተደላደለ ህይወት ለመኖር ከተመኘን በማንኛውም ጉዳይ ላይ አሏህን ልንፈራ ይገባል። እራሳችነንም ከሃጢያት ልንጠብቅ ፣ የጌታችነን ትዕዛዝ አጥብቀን ልንይዝ ፣ ከከለከላቸው ነገሮች ልንርቅ ፣ ቅጣቱን ሊያስከትሉብን ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ እራሳችነን ልንጠብቅ ይገባል።

## 2 ወደ አሏህ መመለስና የአሏህን ምህረት መለመን

አሏህ ስለ ነብዩ ኑህ(ዐ.ሰ) ሲያሳውቀን እንዲህ አለ፡-

**=<({አል-ቁርአን 71:10-12})>=**

**{10} ከጌታችሁ ምህረት ለምኑ፤ እሱ በጣም መሐሪ ነውና በላቸው።**

**{11} በእናንተ ላይ በቂ ዝናብ ያወርዳል።**

**{12} ገንዘብና ልጆችም ይለግሳችኋል። ለእናንተም አትክልቶችን ያደርግላችኋል። ለእናንተም ወንዞችን ያደርግላችኋል።**

ኢማም ኢብን ከሲር ይህን ሲተነትኑ እንዲህ አሉ፡- ወደ አሏህ ከተመለሳችሁ ፣ ምህረትንም ከለመንችሁትና ለትዕዛዙም ተገዥ ከሆናችሁ ሲሳያችሁን ይጨምርላችኋል፤ ከሰማይም ሲሳይን ያወርድላችኋል እንዲሁም ከምድርም አዝዕርትን ያበቅልላችኋል ፣ ከእንስሳቶቻችሁም የወተት ምርትን ይጨምርላችኋል። ልጅና ሃብት ንብረት ይሰጣችኋል። ወንዞች በስራቸው የሚፈሱባቸው የሆኑና የተለያዩ ፍራፍሬዎችን የያዙ የአትክልት ቦታዎችንም ያስገኛችኋል አሉ። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 11:3})>=**

**{3} ጌታችሁን ምህረት ለምኑት። ከዚያም ወደ እሱ ተመለሱ። እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ መልካምን መጥቀም ይጠቅማችኋልና። የትሩፋትንም ባለቤት ሁሉ ችሮታውን ይሰጠዋል። ብትሸሹም የታላቁን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ።**

በተውበት ወደ አሏህ ከተመለስንና ምህረቱንም ከለመነው መልካም ነገር እንደሚሰጠንና ሲሳያችነን እንደሚጨምርልን ቃል ገብቷል።

በአህመድና በአቡዳውድ በተዘገበው ሐዲስ

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አሏህ ምህረቱን አብዝቶ ለሚጠይቀው ከሃዘኑ ሁሉ ያሸለዋል። እንዲሁም ከችግሩ ሁሉ ሚወጣበትን መንገድ ፍፁም ባልጠበቀው መልኩ ያስገኝዋል ብለዋል።

ለምህረት የምንጠይቀው ፀሎት ስንቅን ወይም ሲሳይን ያመጣል ፣ ይጨምርልናል ወይም ይባርክልናል። ይህ የሚሆነው ግን የምናደርገው ፀሎት ከልባችን ከሆነና ሃጢያት መፈፀም ካቆምን ነው። ነገርግን ባፉችን ምህረት እየለመን በጎን የተለያዩ ሃጢያቶችን የምንፈፅም ከሆነ ፀሎታችን ከልብ አይደለም፤ ሆኖም ፀሎታችን ፍሬ ቢስ ነው የሚሆነው።

አሏህ የምንፈልገውን ነገር እንዲያስገኝን ወደ ተውባ እንገስግስ፤ ንግግራችነንም በተግባር እናስከትል። በምላሳችን ብቻ ዱአ ከማድረግ እንጠንቀቅ። ምክኒያቱም ይህ የውሸታሞች ተግባር ነውና።

**3 በአሏህ ላይ መመካት**

**=<({አል-ቁርአን 65 :3})>=**

**{3} ካላሰበው በኩል ሲሳይ ይሰጠዋል። በአሏህ ላይ ለሚመካ ሰው እሱ በቂው ነው። አሏህ ፈቃዱን አድራሽ ነው። በእርግጥ አሏህ ለሁሉም ነገር የተወሰነ ጊዜን አድርጓል።**

ጥቅም ለማግኘትና ከጉዳት ለመጠበቅ ልባችን በአሏህ ላይ ብቻ ተስፋ የምታደርግ ከሆነና ሙሉ በሙሉ በእሱ ላይ ከተመካን ያለብንን ችግር ፣ ሃዘናችነንና ጭንቀታችነን አስወግዶ ሲሳያችነን ባልጠበቅነው መልኩ ይለግሰናል፤ ባለን ነገር ላይም በረካውን ያደርግልናል።

በአህመድና በትርሚዚ በተዘገበው ሐዲስ

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በአሏህ ላይ ሊመኩበት እንደሚገባ በእሱ ላይ ከተመካችሁ ለአዕዋፍት (ሲሳያቸውን) እንደሚያስገኛቸው ለእናንተም ያስገኛችኋል። ጠዋት ባዶ ሆዳቸውን ሆነው ወተው ይሄዳሉ (ሲመለሱ) ሙሉ ሆኖ ይመለሳሉ ብለዋል።

ኢብን ረጀብ በዚህ ሐዲስ ላይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ይህ ሐዲስ በአሏህ መመካት ጉዳይ ላይ መሰረታዊ የሆነ ሐዲስ ሲሆን ሲሳይ ለማግኘት ምክኒያት ከሆኑት አንዱና ትልቁ በአሏህ ላይ መመካት ነው ብለዋል።

በአሏህ ላይ መመካት ሙሉበሙሉ በእሱ ላይ ብቻ ጥገኞች የመሆናችን መገለጫ ነው። ምክኒያቱም የፍጥረታቶቹ ጉዳይ በእሱ ፈቃድ ስር ስለሆነና በዚህ ፍጥረተ አለም ላይ የመቆጣጠር ፣ የማስተናበር ሃይሉም ብልሃቱም ያለው እሱ ብቻ ነውና። እሱ ብቻ ነው የሚያስገኘው ፣ የሚፈጥረው ፣ የሚሰጠው ፣ በረካውን የሚነሳው ፣ የሚጠቅመው ፣ የሚጎዳው ፣ ጤናን ፣ ህመምን ፣ ህይወትን ፣ ሞትን ሁሉ የሚደርገው እሱ አንድ አሏህ ብቻ ነው።

በአሏህ ላይ መመካት አለማዊ የሆኑ ሰበቦችን አለመጠቀምን አያጠቃልልም። ምክኒያቱም አሏህ በእሱ ላይ ከመመካት ጋር ሊሆኑ የሚችሉ ሰበቦችን እንድናደርስ አዞናልና። አለማዊ የሆኑ ሰበቦችን ለመጠቀም ጥረት ማድረግ በእርግጥ አሏህን የመታዘዝ ተግባር ሲሆን በልብ እሱ ላይ መመካት ደግሞ እሱ ላይ ያለንን እምነት የሚገልፅ ነው። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<(﴿አል-ቁርአን 62:10﴾)>=**

## ﴿10﴾ (የጁምአ) ሶላት ባበቃ ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፤ የአሏህንም ችሮታ (በመስራት) ፈልጉ።

እኛ ሙስሊሞች ሁሉንም ሰበቦች ወይም መንገዶች መጠቀም የሚኖርብን ሲሆን ውጤት ያስገኙናን ብለን ግን በእነሱ ላይ አንመካም። ይልቁንም ጉዳዩ ሙሉ በሙሉ ከአሏህ ነው ብለን ማመን ይኖርብናል። አስገኙ እሱ ብቻ ነውና።

## 4 ዝምድናን መቀጠል

ዝምድናን መቀጠል የሲሳይ ወይም የበረከት ምንጭ መሆኑን የሚያረጋግጡ በርካታ ሐዲሶች አሉ።

በቡኻሪ በተዘገበው ሐዲስ

አቡ ኹረይራ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሲሳዩን ለመጨመር የሚፈልግና ከሰዎች መካከል በደግነት (በርህራሄ) መጠቀስ የሚፈልግ ሰው ከዘመዶቹ ጋር ያለውን ግንኙነት ይጠብቅ (ዝምድናን ይቀጥል) ብለዋል።

በአህመድ በተዘገበው ሐዲስ መሰረት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከዘመዶቻችን ጋር ያለን መልካም ግኑኝነት በርካታ ፍሬዎችና መልካም ውጤቶች እንዳሉት አብራርተዋል። ሲሳይ ይጨምራል ፣ እድሜን ያረዝማል ፣ በወዳጅ ዘመዶች መካከል ያለውን ውዴታ ይጨምራል። ታዲያ ዘመድ ማለት ምን ማለት ነው? ዝምድናን እንዴት መቀጠል እንችላለን?

ዘመድ ማለት ሙስሊም የሆኑም ሆነ ያልሆኑ ደም ወይም ጋብቻ የሚያስተሳስራቸው ሰዎች ማለት ነው። ዝምድናን በብዙ መንገዶች መቀጠል ይቻላል። ለምሳሌ በመጠየቅ ፣ ስጦታ በመስጠት ፣ ስላሉበት ሁኔታ በመጠየቅ ፣ የተቸገሩትን በመርዳት ፣ ደግና ሰው አክባሪ በመሆን ፣ ግብዣችን ላይ በመጥራት ፣ እንግዳ ተቀባይ በመሆን ፣ የግብዧ ጥሪያቸውን በመቀበል ፣ ሲታመሙ በመጠየቅ ፣ በችግራቸውና በጭንቀት ጊዜያቸው በማፅናናትና በማገዝ ፣ ለእነሱ ዱአ በማድረግ ፣ በመልካም በማዘዝና ከመጥፎ በመከልከል ወ.ዘ.ተ

## 5 ለአሏህ ብሎ መለገስ(መስጠት)

በአሏህ መንገድ ለእሱ ብለን መለገስ ሲሳያችነን የምንጨምርበት መንገድ እንደሆነ በተለያዩ የቁርአንና የሱና ንግግሮች ተገልፃል። አሏህ እንዲህ ብሏል፡-

**=<({አል-ቁርአን ሳባ :39})>=**

**{39} በል በእርግጥ ጌታየ ሲሳይን ከባሮቹ መካከል ለሚሻው ሰው ያሰፋል፤ ለእሱም ያጠባል። ከማንኛውም የምትለግሱትን እሱ ይተካዋል። እሱም ከሲሳይ ሰጭዎች ሁሉ በላጭ ነው።**

ኢብን ከሲር ይህን አያ ሲተነትኑ ይህ ማለት አሏህ ባዘዛችሁ ወይም በፈቀደላችሁ ቦታ ለምትለግሱት ማንኛውም ነገር በዚህ አለም ህይወት ይተካላችኋል፤ በአሂራ ትመነዱበታላችሁ ብለዋል። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 2:267-268})>=**

**{267} እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ካፈራችሁትና ከዚያም ከምድር ካወጣንላችሁ ከመልካሙ ለግሱ። መጥፎውንም ለመስጠት አታስቡ። በእሱ አይኖቻችሁን ጨፍናችሁ እንጅ የማትወስዱት ስትሆኑ ከእሱ(ከመጥፎ) ትሰጣላችሁን አሏህም ተብቃቂ ምስጉን መሆኑን እወቁ።**

**{268} ሰይጣንም (እንዳትለግሱ) ድህነትን (ማጣትን) ያስፈራችኋል፤ በመጥፎም ያዛችኋል። አሏህም ከእሱ የሆነን ምህረትና ችሮታ ሊሰጣችሁ ቃል ገብቶላችኋል። አሏህም ችሮታው ሰፊ የሆነ ሁሉን አዋቂ ነው።**

ኢብን አባስ(ረ.ዐ) ሁለት ነገሮች ከአሏህ ሲሆን ሁለት ነገሮች ደግሞ ከሸይጧን ናቸው አለ። ሸይጧን ሃብት ላንተ አስፈላጊ ነውና አትለግስ አጥብቀህ ያዝ በማለት ወደ መጥፎ ነገር ያዛል። አሏህ ለወንጀላችን መሃርታ ለማድረግና ሲሳያችን ላይ በረካ ለማድረግ ቃል ገብቷል ብሏል።

## 6 ሐጅና ኡምራ ደጋግሞ ማድረግ

በትርሚዚና በነሳኢ በተዘገበው ሐዲስ

ኢብን መስኡድ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ሐጅና ኡምራን ደጋግማችሁ አድርጉ ምክኒያቱም ድህነትንና ሃጢያትን ያስወግዳል። ልክ እሳት በብረት ፣ በውርቅና በነሃስ ላይ ያለን ቆሻሻ እንደሚያስወግደው ሁሉ። በትክክል የተደረገ ሐጅም ከጀነት ያነሰ ምንዳ የለውም ብለዋል።

## 7 ለደካሞች ደግ መሆን

ሰዎች በመካከላቸው ላሉ ደካሞች ደግ በመሆን ሲሳይና ድል እንደሚያገኙ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ተናግረዋል።

በአቡዳውድና በትርሚዚ በተዘገበው ሐዲስ

አብ ደርዳ(ረ.ዐ) እንዳስተምሯው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በእናንተ መካከል ያሉ ደካሞችን ተንከባከቡ  ሲሳይና ድልን ታገኛላችሁና ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ብሏል።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ደካማ ብለው የገልፃቸው የተለያዩ አይነት ሰዎችን ነው። ለምሳሌ ድሃ ፣ ረዳት የሌላቸው ፣ የሙት ልጆች ፣ ህሙማን ፣ ባሪያዎችን ነው። ታዲያ ለእነዚህ ደግነትን የምናሳይበት መንገድ እንደ ሁኔታው ይለያያል። ድሆችን በገንዘብ በመስጠት፤ የሙት ልጆችን እንዲጠበቁ በማድረግና በገንዘብ በመርዳት፤ ህሙማንን በመጠየቅ ወ.ዘ.ተ

ውድ ሙስሊም እህት ወንድሞቼ! ሲሳያችነን ለመጨመርና የአሏህን እርዳታ ለማግኘት ከፈለግን ለደካሞች ደግ እንሁን፤ በማንኛውም መንገድ እነሱን ከመጉዳት እንጠበቅ።

## 8 እራስን ለአሏህ ማስገዛት

በትርሚዚና በኢብን ማጃ በተዘገበው ሐዲስ

አቡ ኹረይራ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሃያሉ አሏህ የአደም ልጆች ሆይ! ለእኔ እራሳችሁን አስገዙ ልባችሁን በደስታ እሞላላችኋለሁ፤ ሃብታምም አደርጋችኋለሁ። ካልሆነግን ህይወታችሁን የግርግር ህይወት አደርገዋለሁ፤ ድሃም አደርጋችኋለሁ ብሏል ብለዋል።

በዚህ ሐዲስ እራሳችነን ለአምልኮተ አሏህ የምናስገዛ ከሆነ አሏህ ሁለት ነገሮችን ቃል ገብቶልናል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ደስታና ሃብት ሲሆኑ አሏህ ደስተኛ ልብ ከሰጠን ድህነት ወደ እኛ የሚደርስበትን መንገድ አያገኝም። ሆኖም እራስን ለአሏህ ማስገዛት ማለት ሲሳይን አለመፈለግ ፣ ሰበቦቹን አለማድረስ ፣ አለመስራት ወይም መስጊድ ቀንም ለሊትም መቀመጥ ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርብናል።

<u>ሲሳይ ከምናገኝባቸው ሌሎች መንገዶች መካከል</u>

9 ለአሏህ ብሎ መሰደድ

10 ለአሏህ ብሎ ጅሃድ ላይ መሳተፍ

11 ትዳር

12 ለአሏህ አመስጋኝ መሆን

13 ዱአ ማድረግ

14 ከሃጡያት በመራቅ እራስን ለኢስላም ማስገዛት

የመጨረሻው መንገድ ከተገለፁት ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክኒያቱም ሲሳይ የምናገኘው ወይም ሲሳያችን ላይ በረካ ሊኖረው የሚችለው አሏህን ስንታዘዝ ሲሆን ሲሳያችን የሚነሳው ወይም በረካ የማይኖረው ደግሞ እራሳችነን ለአሏህ ተገዥ ሳናደርግ ስንቀር ነው። ሃጢያት መፈፀም ሲሳይ ለማጣት ፣ ለህይወታችን መመሰቃቀል ፣ በረካ ለማጣት ትልቁ ምክኒያት ነው። አሏህ እንዲህ ብሏል፡-

**=<({አል-ቁርአን 72:16})>=**

**{16} እናም በመንገዲቱ ላይ ቀጥ ባሉ ኖሮ በቂ ውሃ(ዝናብ) በሰጠናቸው ነበር።**

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። ተጨማሪ የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!